PANORAMA # XXXVII

**የትዝብት አድማስ**

**ሐምሌ  9 ቀን** 2000 **ዓም**

**ይፈሩታል እንጂ ለምን አይፈሩትም**!

**ፀሀይ በበረቀ  ጀምበር በጠለቀ ቁጥር መለስና ጓደኞቹ የሚያስበረግጋቸው÷ የሚያባንናቸውና የሚያርበተብታቸው ነገር ቢኖር÷ የኢሕአፓ ስም መሆኑ በአሁኑ ወቅት ዓለም ያወቀው ፀሀይ የሞቀው ሀቅ ሆኗል። ይህንን ሀቅ ደግሞ እንኳንስ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ÷ የውጭ ኃይሎች እንኳን ቢሆን በሚገባ ተገንዝበውታል። የውጭ መንግሥታት÷ በኢትዮጵያ የተመደቡ የውጭ ሀገር አምባሳደሮች÷ ዲፕሎማቶች÷ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች÷ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የኢትዮጵያን ጉዳይ በቅርብ የሚከታተሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ሁሉ ሳይቀሩ÷ መለስ ዜናዊ÷ ከማነኛውም የፖለቲካ ተቃዋሚ በበለጠ ኢሕአፓን እንደሚጠላ÷ እንደሚፈራና  ስሙ ሲጠራበትም አረፋ እንደሚደፍቅ በመገረም ይናገራሉ። የኢሕአፓ መልዕክተኞች÷ ለዲፕሎማቲክ ተግባር  በየቦታው በሚንቀሳቀሱበት ጊዜና ቦታ ሁሉ ከሚጠየቁት ተደጋጋሚ ጥያቄዎች የመጀመሪያው÷ “ ኸረ ለመሆኑ÷ መለስ ዘናዊ የኢሕአፓ ጉዳይ ሲነሳበት÷ ፊቱ ሁሉ የሚለዋወጥበት ምክንያቱ ምንድን ነው?” የሚል ነው። መለስ ዜናዊ÷ ለቅርብ አማካሪዎቹና ጋሻ ጃግሬዎችም “ እኛና ኢሕአፓ በአጥፊና ጠፊ ደረጃ ስለሆን ÷በምንም ሁኔታ ከዚህ ድርጅት  ጋር የምንወያይበት የምንቀራረብበትም ሆነ  ዓይን ለዓይን የምንተያይበት ተዓምር ሊመጣ  አይችልም” ብሎ እንደተናገረ ÷ በየጊዜው ከወያኔ ድርጅት ከድተው የሚወጡ ግለሰቦች ሳይቀሩ የሚናገሩት ዕውነታ ነው። ፍራቻና ጥላቻ**

ተጣምረው ሲገኙ መለስ በኢሕአፓ ላይ የወሰደውን ውሳኔ እንደሚወልዱ ይህ ተጨባጭ ማስረጃ ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ÷ መለስ ዜናዊና ድርጅቱ÷ ኢሕአፓን አስመልክቶ÷ ይህንን አቋም ቢወስዱ ሊያስደንቅ አይችልም:: ምክንያቱም÷ ወያኔና ኢሕአፓ ከመጀመሪያው ቢሆን÷ የማይስማሙበት መሠረታዊ ልዩነት ስለአላቸው ብቻ ነበር:: ይህ መሠረታዊ ልዩነት ደግሞ አንዳንዶቹ እንደሚወሽክቱት÷ የሥልጣን ሽኩቻ÷ የወንበር ጉሽምታ÷ የመሪዎች ኩርፊያ÷ የድርጅቶቹ ጥልፊያ÷ የዘር ጥላቻ÷ ወይም የታሪክ ሺሚያ ወይም ደግሞ÷ የህብት ዝርፊያ አልነበረም:: አሁንም አይደለም:: ልዩነት ከዚህ ትርኪ ምርኪ በላይ የሆነ የጠነከረና የተለየ ነው::

በወያኔና በኢሕአፓ መካከል ያለው ልዩነት ዋናው መንስዔ÷ የኢትዮጵያ መኖር አለመኖር ጉዳይ ነው:: ይህ ልዩነት÷ በአንድ በኩል÷ ጥንታዊቷ ኢትዮጵያና ዜጎቿ÷ በዘር በቋንቋና በሃይማኖት ሳይከፋፈሉ÷ ምን ጊዜም አብረው መኖር ይችላሉ÷ የህገራችንና የሕዝቦቿ አብሮ መኖርና አለመኖር÷ ከሁሉ በፊት መሠረታዊ ጉዳይ ነው የሚለውና÷ በሌላ በኩል ደግሞ÷ ለኢትዮጵያ ኅልውናም ሆነ ለዜጎቿ አብሮ መኖር ቅድሚያና መሠረታዊ መሆኑን ያላጤነ÷ ብሎም ዜጎቿ በብሄረሰብ መከፋፈል አለባቸው የሚል ውሳኔ ናቸው:: ይህ እንደ ብርሃንና ጨለማ የተፃረረ ልዩነት÷ የኢሕአፓና የወያኔ ልዩነት ነው:: በምንም ዓይነት መንገድ ሊጣጣም ቀርቶ ሊቀራረብ የሚችል አልሆነም:: አይሆንምም:: "ለእኛ ለወያኔዎች ያልሆነች ኢትዮጵያ÷ ትጥበጣጠስ" በሚሉት በነ መለስ ዜናዊና÷ ምንም-ምን ቢሆን÷ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ መፈራረስ የለባቸውም በሚለው በኢሕአፓ አቋም መካከል ያለ ልዩነት ነው::÷ በመሆኑም÷ መቸም መች ቢሆን÷ ኢሕአፓና ወያኔ ሊስማሙ አለመቻላቸው ሊያስደንቅ
ከቶ አይገባውም:: ሊያስገርምና እንደ ተዓምርም ሊቆጠር የሚችለው ግን÷

ከሁለት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ወይም ሌላው ክስተት ቢመጣ ነበር:: ይኸውም፥ ወይ እነመለስ ዜናዊ ከያዛቸው የጥፋት አባዜ ተላቅቀው፥ ለኢትዮጵያ ኅልውናና ለሕዝቦቿ አብሮ መኖር ሲያስቡና ሲሰሩ፥ ይህ ካልሆነ ደግሞ፤ ኢሕአፓ የቆመበትን ዓላማ ሽጦ፥ በኢትዮጵያ መሠረታዊ ጥቅምና ኅልውና በዜጎቿም ብሔራዊ አንድነትና የግዛት ልዕልና ተደራድሮ ሲገኝ ብቻ ነው:: ይህ መሠረታዊ ልዩነት አግጥጦ-አፍጥጦ በአለበት ሁኔታ፥ በዕርግጥም፥ መለስ ዜናዊ ተናገረ እንዳተባለው፥ ወያኔና ኢሕአፓ በአጥፊና ጠፊ መፈረጃጀታቸው የተፈጥሮ ህግ ነው:: ምክንያቱም፥ አጥፊና ጠፊ ተስማምተው አብረው ለመኖር ስለማይችሉ ነው:: እስካሁን እንደተገነዘብነው ከሆነ ደግሞ፥ መለስና ተከታዮቹ ሲፈጠሩ ጀመረው ከያዛቸው የዘር በሽታ ተፈውሰው፥ ለመላዋ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅምና ለዜጎቿ አንድነት ለማሰብ ተለውጠዋል ብሎ ለማመመን የተዘጋጀ ኢትዮጵያዊ ሊኖር አይችልም::

በሌላ ገፅታ ደግሞ፥ ኢሕአፓ፥ ከመጀመሪያው- ከጥንቱ-ከጧቱ የተመሠረተበትን ዓላማና ለዚህም ሲል የከፈለውን መስዋዕት ገደል ጨምሮ፥ ነገር-ዓለሙን ጠብ-ርግፍ አድርጎ ትቶ፥ በትግሉ ርዝማኔ፥ ተስፋ ቆርጦና ተሽመድምዶ ለሥልጣን ፍርፋሬ ቋምጦ፥ በኢትዮጵያ ስትራተጂያዊና ብሔራዊ ጥቅም ተደራድሮ፥ ከወያኔ ጋር ተሞዳምዶ ይታረቃል ተብሎ አይሞከርም:: አይታሰብምም:: ኢሕአፓ ከወያኔ ጋር ሊሞዳሞድ የሚችለው፤ ቆራጥ አባላቱ ክንዳቸውን ሲንተራሱ ብቻ ይሆናል! ፈረንጆቹ " በሬሳዬ ላይ ብቻ ነው" እንደሚሉት ዓይነት ማለት ነው!

ይህም ነው መለስና ግብረ-አበሮቹ፥ ኢሕአፓን የሚጠሉትም የሚፈሩትና መለስ ዜናዊም ፓርቲውን "ለማጥፋት" የሚፈጨረጨረው:: በሁለቱ ድርጅቶች መካከል ከነበረውና አሁንም ካለው በኢትዮጵያና ሕዝቦቿ መኖር አለመኖር መሠረታዊና መተከላዊ የአቋም ልዩነት ባሻገር፥ ሌሎችም የማይታረቁ ልዩነቶች አሉ:: እነኝህም እንደዚሁ ቀላል ልዩነቶች ሳይሆኑ፥ መሠረታዊ፥

መተከላዊና  ዓይነተኞች ናቸው:: በዘር ላይ የተመሠረተ ሥርዓተ-መንግሥትን ከማምጣት አንስቶ፥ ዘረኛ ሥርዓትን መሠረት ያደረገ "ሕገ መንግሥት" መቅረፅን አካትቶ፥ በዚህም ብልሹ ሕገ መንግሥት ላይ ተመርኩዞ የተቋቋመው አስተዳደራዊና የጎሳ ፌዴራላዊ  አወቃቀርም ሆኑ ፖሊሲዎችና አፈፃፀማቸው ሁሉ ሲጠቃለል፥ የኢትዮጵያን ብሔራዊና ስትራተጂያዊ ጥቅሞችን የሚጎዱና የጎዱ ለመሆናቸው፥ የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የሚመሰክረው ሀቅ ነው:: በዚህ ብልሹና አጥፊ አገዛዝ ላይ ተመርኩዘው የሚወጡት ማነኛቸውም ፖሊሲዎችና አተረጓጎማቸው፥ ሀገራችንን በዘለቄታ መልኩ ለማጥፋትና ሕዝቡንም ለመከፋፈል የተወጠኑ ሴራዎች ውጤት ናቸው ብሎ ስለሚያምን፥ በዚህም ነጥብ ላይ ኢሕአፓ ከወያኔ ጋር የማይታረቅ ዓቢይ ቅራኔ አለው:: ይህም ለመለስ ዜናዊና ኩባንያው ኢሕአፓን ለመጥላት፥ ለመፍራትና ለመርበትበት ተጨማሪ ምክንያት ሆኗቸዋል::

በተጨማሪ የኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ኃብት፥ ማለትም፥ ከመሬት በላይም ይሁን በከርሰ-ምድሯ ያለው ዕምቅ ኃብት፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ የሚያዝበት፥ የሚጠቀምበትና የሚቆጣጠረው ብሔራዊ ኃብቱ እንጅ፥ የጥቂት ወገኖች የተለየ የግል ኃብት ሊሆን ይገባል ብሎ ኢሕአፓ አያምንም:: ይህ ብሔራዊ ኃብት ደግሞ፥ በጋራና በዕኩልነት ለሁሉም ዜጋ ሊያገለግልና ሊጠቅም ይገባል፥ይችላልም ብሎ  ያምናል:: ድኅነት የሚወገደው፥ ዕድገት የሚመጣውና ሕዝቡንም በዕኩልነት አንድነቱን ጠብቆ በሠላም ሊኖር የሚችለውም ይህ ዕውን ሲሆን ብቻ ነው:: ይህን አቋም የወያኔ መሪዎች አይወዱትም:: ምክንያቱም ይህ የኢሕአፓ መተከላዊ አቋምን መለስ ዜናዊ እንደ ጉሮሮ አጥንት ስለሚያንቀው ነው:: "ወይ አይበላ ወይ አያስበላ" ዓይነት ነገር ሆኖበታል::  መለስና ባልደረቦቹ፥ "ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል" ባዮች ናቸው:: "ሞኝ አሳለፌ ዘመዱን ይጎዳል እንዳንባል፥ ዛሬ በሥልጣን እያለን ወገናችችን ካልጠቀምን ምን ዋጋ አለው" ብለው የሚያምኑ ከንቱና የከንቱ ከንቱ ሆነዋል:: ይህ ፍሬ ከርስኪ አመለካከትና አሳፋሪ ድርጊት የኢሕአፓ አጀንዳ  ባለመሆኑ፥

ወያኔዎች ፓርቲዉን እንዲጠሉት ሌላ ተጨማሪ ምክንያት ሆኗቸዋል።

በኢሕአፓ ዕምነት፥ ሀገራዊ ነፃነትም ይሁን የሕዝብ ሉዓዋላዊነት፥ የኢኮኖሚ ዕድገትም ይሁን ብሔራዊ ብልፅግና የሚመጣው፥ የዴሞክራሲ ሥርዓት ሰፍኖ በተግባር ሲተረጎም ብቻ ነው። የዲሞክራሲ ሥርዓት መረጋገጥ ደግሞ፥ለሰላም ዋስትና ከመሆኑ በላይ፥ ሕዝቡም ገላውን ሰዶ ፥ በልማቱ ሂደት ውስጥ ሙሉ ተሳታፊ የሚሆንበት ዕድል ያገኛል። የወያኔ መሪዎች ይህ አይዋጥላቸውም። በሰላም ፋንታ ብጥብጥ፥ በመረጋጋት ፋንታ ሽብርን ይመርጣሉ። ለዚህም የራሳቸው ምክንያት አላቸው። ሕዝብ መረጋጋትና ሰላምን ካገኘ ፥ ጊዜና ፋታ ስለሚያገኝ፥ ለመቃወም ኃይል ያገኝብናል ብለው ስለሚፈሩና ስለሚጨነቁ ብቻ ነው። በመሠረቱ የወያኔ መሪዎች የሚጠሉት የሚፈሩትና የሚያርበተብታቸውም ኢሕአፓ ብቻ ሳይሆን፥ዋናው ምልዐተ ሕዝቡንም ጭምር ነው።ኢሕአፓን የሚጠሉትም የሕዝብ ድጋፍ ስላለው ነው። በመሆኑም የሕዝብ ወገን የሆነውን ኃይል ሁሉ ይፈሩታል ይጠሉታል። በዚህ መንስዔ ፥ኢሕአፓ በወያኔ በኩል እንደ አጥፊና ጠፊ መፈረጁ የማያስደንቀውም ለዚሁ ነው። ኢሕአፓ ከፅንሱ እስከ ዕድገቱ፥ በትግል ሂደቱ ሕይወቱም ሆነ ራዕዩ ብሔራዊ ነው። ይኸም ሊሆን የበቃው፥ ከሰፊው የኢትዮጵያ ማህፀን ተፀንሶ፥ ከኢትዮጵያ አብራክ የተወለደ በመሆኑ ነው። ከዚህ ሰፊ የኢትዮጵያ ማኅፀን በመወለዱም ዓላማውና ራዕዩ ብሔራዊ ነው። ከሁሉም የውልደትና የመደብም ጀርባ የመጡ አባላቱም፥ ለመላዋ ኢትዮጵያ ሀገራዊ ጥቅምና ክብር፥ ነፃነትና ብልፅግና ሲሉ መሰዋታቸውና መሰቃየታቸው አያስደንቅም። ይህም ዕውነታ ወያኔንና ኢሕአፓን የሰማይና የምድር ያህል ያራርቃቸዋል። ለአንድ ብሔር ጥቅም ሲል የተመሠረተና የተፈጠረ ጠባብ ብሔረተኛ ቡድንና፥ ለመላዋ ኢትዮጵያ ክብርና ጥቅም ሲል ተመሥርቶ የሚታገል ሀገራዊ ዓለማን አንግቦ የቆመ ኅብረ-ብሔር ድርጅት ኢሕአፓ፥ የማይታረቅ የዓላማና የራዕይ ልዩነት ስላላቸው፥እነ መለስ ዜናዊ የኢሕአፓ ስም ቢያስደነግጣቸው፥ ቢያርበተብታቸውና አረፋ ቢያስደፍቃቸው ምን ያስገርማል?

ኢሕአፓንና ወያኔን ተፃራሪ ከሚያደርጋቸው መሠረታዊ ጉዳዮች መካከል ሌላው ዓይነተኛ ልዩነት አንዱ፥ ኢትዮጵያን ከውጭ ኃይሎች ተገዥነትና ተጽዕኖ ነፃ የሆነች ሀገር ማድረግ በሚለው ላይ ነው። የኢሕአፓ የውጭ ጉዳይ መመሪያ ነፃና በገለልተኛነት ላይ የተመሠረተ ፓሊሲ ማካሄድ ሲሆን፥ ወያኔዎቹ ግን ሀገራችንን ለምዕራባውያን ቅኝ ተገዥ አድርገዋታል። እኛ የሀገራችንን ነፃነትና ልዕልና ኅልውናም ይሁን ሰብዕና በምንም ዓይነት መንገድ ፥ ለባዕድ ተገዥ የሚያዳርጋትን ፖሊሲ የምንቃወምው ነው። የባዕዳንን ጥቅም በማስጠበቅና የነርሱንም ርዳታ በማግኘት ሥልጣን ላይ ለመውጣት ሲባል በሀገራችንና በሕዝባችን ነፃነት ፥ ብሄራዊ ጥቅም፥ የግዛት አንድነትና ልዕልና ላይ መደራደር አንችልም። ለምን ቢባል፥ የኢሕአፓ አባላት የትግላቸው አልፋና ኦሚጋ፥ የሀገራቸውን የኢትዮጵያና የሕዝቧንም ብሔራዊ ጥቅም ማስጠበቅና ማስከበር በመሆኑ ነው።

ታዲያ ዛሬ በድጋሜ፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የምናሳወቅውና የምናመለክተው፥ በወያኔ መሪዎችና በኛ በኢሕአፓዎች መካከል ያለውን የማይታረቅና የማይስማማ መሠረታዊ ልዩነት ምን ጊዜም ቢሆን እንዲረዳልን ብቻ ነው። ለዚህም ዋነኛ ምክንያት መንስዔ የወያኔን ፖሊሲና አሰራር እስከ መጨረሻው የደማችን ጠብታ የምንዋጋውና ትግላችንንም የምናፋፍም መሆናችን እየደጋገምን እናረጋግጣለን። ጠላት እንዲጠላን እንጂ እንዲወደን ፍላጎት ስለሌንም፥ በወያኔ ፀረ ኢሕአፓነት ሕዝባዊነታችንን እያንፀባረቅን ትግላችንን እንቀጥላለን።